

## የተሻሻለ የወተት ከብቶች

# አያያዝ መመርያ

## የጥጃችና ጊደሮች አያያዝ

2010 ዓ.ም

SNV

Designed & Printed by

master print

አራት ኪሎ ፡፡ +251 111 557 788 ገርጂ ፡፡ +251 116 298 777

31362 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

www.masterprintaddis.com

# 1 የጥጆች እና ጊደሮች አያያዝ

**የዛሬ ታዳጊ ጥጆች የነገ ተተኪ የወተት ላሞች ናቸው። በተለይ የጥጆች አያያዝ የጥጆችን ሞት በመቀነስ የወተት ከብት እርባታን ትርፋማ ማድረግ ያስችላል። ጥጆች ለበሽታ እና የተፈጥሮ ጫናዎች (በተለይ ቅዝቃዜ)ተጋላጭ ናቸው።**

በዚህ ክፍል ጥጆች ከተወለዱበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ጊደር እድሜያቸው ድረስ ሊደረጉላቸው ስለሚገቡ ተግባራት ስዕላዊ መግለጫዎች በማስደገፍ በ5 ንዑስ ክፍሎች ተገልጸዋል፡፡



የጠዋት ፀሀይ ለጥጆች ጤንነት አስፈላጊ ነው

## ቁልፍ መልዕክት

የጥጆች አያያዝ ግብ መሆን የሚገባው በመጠነኛ ወጪ የጥጆችን ፈጣን እድገት ማረጋገጥ ነው፡፡ የጥጆችን ሞት መቀነስ፣ ጤነኛ እና ጠንካራ የሆኑ ተተኪ ጥገቶችን ማሳደግ ትርፋማ ያደርጋል፡፡

ጥሩ የጥጆች አያያዝ ጤነኛ፣ ፈጣን አካላዊ እድገት ያላቸው ቁመናቸው የተስተካከለ እና ክብደታቸው ተመጣጣኝ የሆነ ጥጆችን ለማግኘት ያስችላል፡፡ የዲቃላ ጥጆች በሦስተኛ ወራቸው እስከ 90 ኪ.ግ ክብደት ላይ ወተት መጠጣት ሊያቆሙ ይችላሉ፡፡

የጥጆች ማሳደጊያ በረት ለየት ባለ ንፅህና መያዝ አለበት፡፡ ወለሉ ደረቅና ክፍሉም ንፁህ አየር እንደ ልብ የሚያዘዋውር መሆን አለበት። ነገር ግን ንፋስና ከፍተኛ ቅዝቃዜ ለጥጆች ጤንነት አደገኛ ናቸው፡፡

# 1.1 የታዳጊ ጥጆች አያያዝ

**የወተት ልማት ቁልፍ ችግር ከፍተኛ የሆነ የታዳጊ ጥጆች ሞትና ምርታማ የሆኑ ጥጆች የመተካት ችግር ናቸው።**

**ታዳጊ ጥጆች ከተወለዱበት ቀን አንስቶ ጡት እስኪጥሉ ድረስ የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ተገቢ ነው።**

1. ጠንካራና ጤነኛ ጥጆች ለማግኘት እርጉዝ ላሞች ከመውለጃቸው ዕለት 15 ቀናት ቀደም ብሎ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል። የመውለጃ ቦታቸው በንፁህና ደረቅ ጉዝጓዝ (እንደ ጭድ ያለ) ማድረግ አስፈላጊ ነው።
2. ላሟ በምትወልድበት ወቅት እርዳታ ካላስፈለጋት በቀር በተፈጥሮ እንድትወልድ መጠበቅ ያስፈልጋል



3. ጥጃው ከተወለደ በኋላ የአተነፋፈስ ሁኔታውን መከታተል ያስፈልጋል። የማይተነፍስ ከሆነ ሁለት የኋላ እግሮቹን በመያዝ መዘቅዘቅ እንዲሁም በአፍንጫው ቀዳዳ ውስጥ እንደ ቀሰም ያለ ነገር በማስገባት መተንፈስ እንዲችል ማድረግ ያሻል።
4. የጥጃው እትብት ጫፍ በአዮዲን ወይም በአልኮል በመንከር በሽታ አምጪ ተዋሲያን እንዳይገቡ መከላከል ያስፈልጋል።
5. እንገር ወሳኝ በሽታ ተከላካይ ንጥረ ነገር የያዘ በመሆኑ ጥጆች እንደተወለዱ በበቂ መጠን መውሰድ አለባቸው። ጥጃው በተወለደ ከ1-6 ሰዓት ውስጥ እስከ 2 ሊትር እንገር ማግኘት አለበት።
6. ጥጆች ምቾት በሚሰጥ ደረቅ እና ሞቃት በሆነ ቦታ ላይ ማደግ አለባቸው።
7. ለጥጆች የጠዋት ፀሐይ አስፈላጊ ነው በየቀኑ ቢያንስ ለ1 ሰዓት የጠዋት ፀሐይ መሞቅ አለባቸው።
8. ለታዳጊ ጥጆች በተዘጋጀ የተናጠል ጎጆ (nest) እስከ ሁለተኛ ወራቸው ድረስ መያዝ አለባቸው።
9. ጥጆች ለንፋስ ተጋላጭ ባልሆነ ነገር ግን አየር እንደልብ በሚዘዋወርበት ቦታ ማደግ አለባቸው።
10. ጥጆች በተወለዱ ከ15ኛ ቀናቸው ጀምሮ ንፁህ ውሀና ደረቅ መኖ /በተለይ ሳር/ ሊያገኙ ይገባቸዋል።
11. ጥጆች ከእናቶቻቸው ጋር እና እርስ በርሳቸው እንዳይላላሱ መከላከል ያስፈልጋል። ይህ ካልሆነ የፀጉር ኳስ በጨጓራቸው ውስጥ በመፈጠር ለሕመም ያጋልጣቸዋል።
12. ከሁለተኛው ወር ጀምሮ ለጥጆች ወተትን የሚተኩ ምግቦች ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው።
13. የጥጆች እድሜ ከ1-2 ወር ሲሞላቸው ከሚከናወኑ ወሳኝ ተግባራት ውስጥ መለያ ቁጥር መስጠት፣ የቀንድ ስር ማጥፋት፣ ትርፍ ጡቶች መቁረጥ እና ወንድ ጥጆችን መለየት ይገኝባቸዋል።

# 1.2 የእንገር አመጋገብ

**እንገር ላሟ ከወለደችበት እስከ አንድ ሳምንት ድረስ ያለው ወተት ነው። እንገር በንጥረ ነገር ይዘቱ በጣም ከፍ ያለና ከወተት በተለየ ሁኔታ በውስጡ በሽታ ተከላካይ ንጥረ ነገሮች የያዘ ነው።የበሽታ ተከላካይ ንጥረ ነገሮች በጥጃው አንጀት ዘልቆ የሚገባው ግን በ24 ሰዓታት ውስጥ ነው። እንገር ከወተት በላቀ ሁኔታ ከፍ ያለ የቅባት፣ የፕሮቲን፣ የቫይታሚንና ማዕድናት ይዘት አለው።**

**እንገር ጥጃው እንደተወለደ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መሰጠት እንዳለበት እና ላሟ እንገር የማይወጣት ከሆነ ወይም በድንገት እንገር የማይገኝበት ሁኔታ ከተፈጠረ ጥጃውን ለማትረፍ አማራጭ መንገዶችን ማወቅ ያስፈልጋል።**



**ጥጆችን በዕቃ ወተት ለማጠጣት ማለማመድ (ከ1-3)**

1. በመጀመሪያ ሁለት ጣቶችን በወተት /እንገር ውስጥ በመንከር የጥጃው አፍ ውስጥ መጨመር። ይህንን ተግባር መደጋገም፣
2. ቀስ ብሎ ወተት የነካውን ጣት ወተት ወደያዘው ዕቃ ዝግ በማድረግ ጥጃው እስኪለምድ ድረስ ይህንን ተግባር መደጋገም፣
3. የጥጃውን አፍ ወተት ወደያዘው ዕቃ ዝቅ በማድረግ በቀጥታ እንዲጠጣ ማድረግ። የጥጃው አፍንጫ በወተቱ ውስጥ እንዳይጠልቅ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።




## ቁልፍ መልዕክት

- ጥጆች በተወለዱ ከ1 እስከ 6 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ በቂ እንገር ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።
- ጥጃው በቀጥታ ከእናቱ የማይጠባ ከሆነ ከ6-12 ሰዓት ውስጥ በሁለት ጊዜ ሁለት ሁለት ሊትር እንዲጠጣ ማድረግ ያሻል፣
- እንገር መወሰድ ያለበት ካላረጁ ላሞች ሲሆን እንገሩን አልቦ ወዲያው ለጥጆች መሰጠት አለበት።
- ጥጃው ከተወለደ ለ6 ሰዓታት እንገር ሳያገኝ ካረፈደ እስከ 3/10ኛ የሚሆን የበሽታ ተከላካይ ንጥረ ነገር ያጣል። ጥጃው ለ12 ሰዓት ካረፈደ እስከ 6/10ኛ በሽታ ተከላካይ ንጥረ ነገር ያጣል። ይህ የጥጃውን የበሽታ የመከላከል አቅም በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳል/ ይጎዳዋል።

## 1.3 ወተት፣መኖ እና ውሀ ለጥጆች

**ጥጆች ከተወለዱበት ጡት እስከሚጥሉበት (ወተት እስከ ሚያቆሙበት) ዕድሜያቸው ድረስ የሚያስፈልጋቸውን የወተት፣ የመኖና የመጠጥ ውሀ መጠን ማወቅ ከሚያስፈልጋቸው በታች በመስጠት ጥጆች እንዳይጐዱ፣ ወይም ከሚገባቸው በላይ በመስጠት ኪሳራ ውስጥ ላለመውደቅ ይረዳል።**

### ምን ያህል ወተት፣ መኖ እና የመጠጥ ውሀ?

**ውሀ:** በሠንጠረዡ እንደተገለፀው ንፁህ የመጠጥ ውሀ እንደየ ጥጃቹ እድሜ መቅረብ አለበት። በሞቃት ቦታ ጥጆች በሦስተኛ ወራቸው ላይ እስከ 25 ሊትር በቀን ሊወስዱ ይችላሉ።

**ወተት:** ወተት ለጥጆች ሙሉ እና አስፈላጊ ንጥረ ነገሮችን ሁሉ ማለትም በቂ ሐይል ሰጪ፣ ፕሮቲን፣ ማዕድናት ቫይታሚኖችና ውሀ የያዘ ነው። ጥጆች የክብደታቸውን 1/10 ያህል ወተት በየቀኑ ቢሰጣቸው ለዕድገታቸው ተመራጭ ነው። ነገር ግን የወተት ዋጋው ከፍ ያለ ስለሆነ ቀስ በቀስ ወተትን በሌሎች መኖዎች መተካት ርባታውን አዋጭ እንዲሆን ያደርገዋል።

| የመኖ ዓይነት | አስፈላጊ የመኖ መጠን በጥጆች ዕድሜ ክልል ለዲቃላ ጥጆች | | |
|---|---|---|---|
| | 0-15 ቀን | ከ3-8 ሳምንት | ከ9-12 ሳምንት |
| ወተት | ከ2-3 ሊትር | ከ 3-4 ሊትር | ከ 1-2 ሊትር |
| የመጠጥ ውሃ | | ከ10-15 ኪ.ግ | ከ15-25 ኪግ |
| ምጥን መኖ | | ከ0-5 ኪ.ግ | ከ1-1.5 ኪ.ግ |
| ሳር | | በፈቀዱት ልክ | በፈቀዱት ልክ |



የክልስ ከብቶች ጥጆች ከ10-12 ሳምንታት ጊዜ ውስጥ ወተት እንዲያቆሙ ለማድረግ እስከዚህ ዕድሜያቸው በቂ ወተት መውሰድ አለባቸው። ተተኪ መኖ ማዘጋጀት ግን በጣም አስፈላጊ ነው።

**የወተት ምትክ:** ወተት ጥጆችን በመመገብ ሊከሰት የሚችል ወጪን መቀነሻ ዘዴ የወተት ምትክ ማዘጋጀት ነው። እንደ አሬራ፣ አጓት፣ የዱቄት ወተት (ዋጋው ከወተት ያነሰ ከሆነ) በመመገብ ወጪን መቀነስ ይቻላል።

**ደረቅ መኖ:** ጥጆች በቶሎ ወተት እንዲያቆሙ በማድረግ ወጪን ለመቀነስ የጥጆች ምጥን መኖ ቢያንስ እስከ 4 ወር እድሜያቸው መመገብ አስፈላጊ ነው። በሰንጠረዡ እንደተገለፀው ከ2-3 ወር ባለው ዕድሜያቸው እስከ 2 ኪ.ግ ምጥን መኖ እንዲመገቡ በማድረግ ጥጆች ሳይጎዱ ወጪ መቀነስ ይቻላል። ከ4 ወራቸው ጀምሮ ግን ጥሩ ሳርና ሌሎች ቅጠላ ቅጠሎችን መመገብ ይገባል።

## 1.4 የጥጆች ጎጆ እና ቤት አሰራር ዘዴ

- ጥጆች ምቾት ባለው፣ ደረቅ(ከእርጥበት ነፃ በሆነ) እና ሞቃት በረት ወስጥ ማደግ አለባቸው
- ጥጆች ከእናቶቻቸው፡ ከሌሎች ጥጆች እና ሰው ንክኪ መራቅ አለባቸው።
- እስከ ሁለት ወር ዕድሜያቸው ድረስ ልዩ በሆነ ለጥጆች በተዘጋጀ ጐጆ እና ከ3-6 ወር ዕድሜያቸው ድረስ በጋራ ሊኖሩ ይችላሉ።



በጥሩ ሁኔታ የተሰራ የጥጆች ጎጆ

- የጥጆች ቤት / ጎጆ ማናቸውም ጋሬጣ ከሚፈጥሩ ነገሮች /እንደ ሽቦ፣ ሚስማር፣ አጉል ጠርዝ ያሉ/፣ እንዲሁም ቅዝቃዜ ከሚያባብሱ የግንባታ መሳሪያዎች / እንደ ሲሚንቶ፣ ብረት ያሉ/ እንዲሁም ወለሉ ከሚያዳልጥ ቤት ነፃ መሆን አለባቸው። ለጥጆች ቤት / ጎጆ/ ተመራጩ እንጨት/ጣውላ ነው።
- ጥጆች ንፋስ እና ቅዝቃዜ አይችሉም፣

## 1.5 የጊደሮች አያያዝና ኮርማ ፍላጎት ዕድሜ

**ጊደሮች የኮርማ ፍላጐት ዕድሜ እና የክብደታቸው መጠን በጊደሮች የፍትወት ዑደት (ሸክርክሪት) የሚጀምርበት ዕድሜ የጊደሮች አያያዝ በሰንጠረዡ እንደተመለከተው የክብደታቸው መጠን እንደየ እድሜያቸው ተመጣጣኝ መሆን አለበት።**



| ዕድሜ | ዝርያ | | |
|---|---|---|---|
| | የሀገረሰብ ዝርያ | ዲቃላ | ዲቃላ |
| ከ 3-9 ወር | ከ 50-80 ኪ.ግ | ከ80-110 ኪ.ግ | 110-130 ኪ.ግ |
| ከ 14-24 ወር | ከ 75-150 ኪ.ግ | ከ 75-150 ኪ.ግ | >200 ኪ.ግ |

## ቁልፍ መልዕክት

- አንድ ዲቃላ ጊደር እንደ ዝርያዋ እና አያያዟ ሁኔታ በአማካይ ከ14-18 ወር ዕድሜዋ ውስጥ የኮርማ ፍላጐት ልታሳይ ትችላለች።
- በአማካይ ከ175-190 ኪ.ግ ክብደት ሲኖራት ወይም የእናቷን 60% ክብደት ስትደርስ ኮርማ ብታነሳ ወይም ብትጠቃ ተመራጭ ነው።
- የኮርማ ፍላጎት ካሳየችበት ሰዓት መጨረሻ ጀምሮ ከ6-12 ሰዓታት ውስጥ ጊደሯን ማስጠቃት ውጤታማ እርግዝና እንዲከሰት ያደርጋል።
- ጊደሮች በተለይ እስከ 12 ወር ዕድሜያቸው ድረስ በጥሩ ሁኔታ ሊያዙ ይገባል። ከሚገባው በታች እንዳይከሱ ከሚገባው በላይ እንዳይወፍሩ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው። አለበለዚያ በእርግዝና ወቅት ችግር ሊገጥማቸው ይችላል።